# ሥርዐተ ትምህርትና መምህሩ

ማረው ዘውዴ (ዶ/ር)*

1. በርዕሱ ወደ ተነሱት ሁለት አብይ ጉዳዮች ከመግባቴ በፊት ሁለቱን ፍዤ ሃሳብ ስለሚያስገኝዋቸው ቁም ነገር አንዳንድ ነገር ማንሳት የሚገባ ይመስለኛል፡፡ ሁሉቱን ፍሬ ሃሳብ የሚያስተሳስራቸው ቁም ነገር የመማር-ማስተማር ሂደት ነው፡፡ አንድ መምህር በብቃት ለማስተማር በሥርዐተ ትምህርቱ የሚነሱ ጉዳዮችን ማወቅና በተግባር መተርጎም ይጠበቅበታል፡፡ ሥርዐተ ትምህርቱም አንድን ትምህርት በብቃት ለማስተማር የሚያስችሉ ጉዳዮችን መለየትና በሥራ ላይ የሚውሉበትን መንገድ መጠቆም አለበት፡፡

2. በአግባቡ የተዘጋጀ ሥርዐተ ትምህርት ውስጥ መማር-ማስተማር ማለት ለተማሪዎቹ ስለ አንድ ነገር መንገር፥ በስሌዳ ላይ ስለአንድ ነገር ጽፎ ተማሪዎቹ እንዲገለብጡ ማድረግ፥ ቱማሪዎች ተራ በተራ እየተነሱ እንዲያነቡ ማድረግ፥ ወይም ትርጉም የሌለው የክፍልና የቤት ሥራ መስጠት አለመሆኑን ይጠቁማል፡፡ ትሩ ሥርሀተ ትምህርት መማር ማስተማር ማለት ተማሪዎች በግል ተነሳሽነት፥ ተሳታፊነት እንዲማሩ ማድረግ መሆኑን ያሳያል፡፡ መምህሩ ለመማር-ማስተማሩ ሂደት አመች ሁኔታ እንዲኖር ዝግጅት እንዲያደርግ፥ ተማሪዎቹ የሚያደርጉትን የትምህርት እንቅስቃሴ እንዲያሳይ፥ እንዲከታተል፥ የትምርቱ ግብ መምታት እንዲገመግም፥ ለሚቀጥለው አቅጣጫ እንዲነድፍ፥ እንዲዘጋጅ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ሁሉ ሥርዐተ ትምህርቱ ይጠቁማል፡፡ መምህሩም ሥርዐተ ትምህርቱን በበለጠ የሚለጽግበትን መንገድ ይቀይሳል፡፡

3. ሥርሀተ ትምህርት ከአንድ አገር የትምህርት ፖሊሲ ላይ በመመሥረት አጠቃላይ የሆኑ ነገሮችን የሚያሳይ የትምህርት አብይ ሰነድ ነው፡፡ አንድን መምህር በበለጠ የሚረዱት ከዚህ ሰነድ የሚመነጩ ሌሎች የትምህርት ሰነዶች ማለትም መርሀ ትምህርት፥ የተማሪው መማሪያ፥ የመምህሩ መማሪያ፥ የትምህርት ደረጃ አጠቃቀም መመሪያ ናቸው፡፡ እነዚህም ለእያንዳንዱ ትምህርት መዘጋጀት አለባቸው፡፡ መምህራንም ዕለት በዕለት እንደጠቀሙባቸው አመች ሁኔታ መፍጠር አለበት፡፡

---

* ተ/ፕሮፌሰር፥ የካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ትምህርት ክፍል፣ ትምህርት ፋኩልቲ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

4. ከላይ የጠቀስኳቸው የሥርዐተ ትምህርትና የመምህሩ ግንኙነት ትርጉም የሚኖራቸውና ውጤት የሚሰጡት መምህርንና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የትምህርት ሰዎች በዝግጅት ጊዜ ተሳታፊ ሲሆኑ ነው። መምህራን ሙሉ በሙሉ፥ ከታች እስከ ላይ፥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እንዲሳተፉ ማድረግ አቅምን ይጠይቅ ይሆናል። ግን በትምህርት ቤት ደረጃ በሥርዐተ ትምህርቱ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩና ሃሳብ እንዲያቀርቡ ማድረግ፥ የተገኙትም አስተያየቶች በተለያየ መንገድ በየትምህርቱ መርሀ ትምህርት፥ በተማሪው መማሪያ፥ በመምህሩ መመሪያ፥ እንዲካተቱ ማድረግ መምህራን አስተዋጽኦቸውን እንዲያዩና ተጣርቶ የቀረበውን መንገድ በሥራ ላይ እንዲያውሉ የማድረግ መሠረታዊ ጠቀሜታ አለው። መምህራን የሚሳተፉባቸውን ጉዳዮች በሚከተለው መንገድ መንደፍ ይቻላል።

*የተማሪ ተኮር የሥርዐተ ትምህርት ዝግጅት ሂደት ባጭሩ*



5. ከላይ የቀረቡት ጉዳዮች በንድፍና በሃሳብ ደረጃ ቀላል መስለው የታዩ ይሆናል። ግን በሥራ ሲተረጎሙ/ተግባራዊ ሲሆኑ እንደማንኛውም ሁኔታ አስቸጋሪ መሆናቸውን እገነዘባለሁ። ነገር ግን እነዚህን አውቆ፥ እቅድ አውጥቶ ጊዜ ወስዶ በተቻለ መጠን መምህራን አሳትፎ ሥርዐተ ትምህርትንና ሌሎችን የትምህርት ሰነዶች ማዘጋጀት ውጤታማ እንደሚሆን የብዙ አገሮች ተመክሮ ያሳያል።